# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 215 ሰኔ 21 2004 ገጽ 1


አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ግንቦት7: የፍትህ፤ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ፤ ወያኔ "የደቡብ ብሄር፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት" እያለ በሚጠራው የአገራችን ክልል ውስጥ የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን ሁሉ በትግራዩ ገዢ ጉጅሌ መሠሪ ተንኮል ሳቢያ ዓይናቸውን ከዋነኛ ጠላታቸው ወያኔ ላይ እንዳይነቅሉ በጥብቅ ያሳስባል።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## ዘረኛውና አምባገነኑ መለስ ዜናዊ በቤልጂዬም ብራስልስ ህክምና ላይ መሆኑ ተሰማ

ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ ከፍተኛ የሆነ የጤንነት መቃወስ የደረሰበት መለስ ዜናዊ በአሁኑ ጊዜ በብራሲልስ ቤልጂዬም ውስጥ ህክም እየተደረገለት መሆኑን ለዝግጅት ክፍላችን የደረሰ መረጃ አመለከተ።

ባለፈው ሳምንት በመክሲኮ ተደርጎ በነበረው የቡድን 20 አባል አገራት ስብሰባ ላይ ለተሳትፎ ብቻ ታይቶ የነበረው መለስ ዜናዊ ከስብሰባ በኋላ አገር ቤት መመለሱን የሚገልጽ ምንም አይነት ኦፍስላዊ ዜና ባለመሰማቱ ብራስልስ ለህክምና የሄደው ከመክሲኮ መለስ በቀጥታ ሊሆን እንደሚችል እነዚሁ ምንጮች ገልጸዋል።

መረጃውን ለማጣራት የዝግጅት ክፍላችን ባደረገው ሙከራ መለስ ለአእምሮ ኢጢ ህክምና በየጊዜው የሚመላለስበትን ሆስፒታል ሃላፊ በስልክ አነጋግረን ከበሽተኛቸው ፈቃድ ውጪ ምንም አይነት መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ እንዳልሆኑ ገልጸዋል።

እንደመረጃ ምንጮቻችን ገለጻ መለስ ዜናዊን ሆስፒታል ያስገባው በሽታ እስካሁን በህክምና ሲረዳ የነበረው የአእምሮ ኢጢ ወደ ካንሰርነት ተሸጋግሮ ነው። ከዚህ በተጨማሪም ለረጂም ጊዜ በምግብና በመድሃኒት ሃይል ሲቆጣጠረው የኖረው የስኳር በሽታ አንዴ ወደላይ ሌላ ጊዜ ደግሞ ወደታች እየወረደ ለመቆጣጠር አስቸጋሪ ሆኖአል ተብሎአል።

የመለስ ዜናዊ ጤንነት በዚህ ደረጃ ላይ መድረስ በህወሃት አመራር ዘንድ ከፍተኛ ድንጋጤ ከመፍጠሩም በላይ ዜናው በመላው አባላቱ ዘንድ ቢሰራጭ የድርጅቱን ሂልውና ሊፈታተን የሚችል አደጋ ሊያስከትል ይችላል ተብሎ ስለተሰጋ ህመሙ የምግብ መመረዝ ነው ተብሎ በየደረጃው ላሉ አባላት እየተነገረ እንደሆነ ለማወቅ ተችሎአል።

መለስ ዜናዊ ታይቶበታል በተባለው የመክሲኮ ቡድን 20 ስብሰባ ላይ ጋዜጣዊ መግለጫ እንኳ ለመስጠት አቅም አንሶት ከህወሃት አንጋፋ አመራር አባላት አንዱ የሆነውና በውጪ ጉዳይ ሚንስቴር ውስጥ ለሃይለማሪያም ደሳለኝ በታኮነት የተመደበው ብርሃኔ ገብረክርስቶስ እርሱን ተክሮ መግለጫ ሲሰጥ ተስተውሎአል።

ባለፈው ሳምንት የመለስ ዜናዊን የተጎሳቀለና የገረጣ ምስል በተለቪዥን የተመለከቱ የህክምና ባለሙያዎች ወደ ካንሰርነት ተቀይሮአል ለተባለው የአዕምሮ ኢጢ በሽታው የኬሞ ቴራፒ ህክምና ሳይጀምር እንዳልቀረ ሙያዊ አስተያየታቸው ሰጥተዋል።

## የዘረኛው መለስ ዜናዊ ፍርድ ቤት በነጻነት ታጋዮች ላይ የጥፋተኝነት ብይን አስተላለፈ። ከሳሾቹ አንድጠጣው የሚፈልጉትን የግፍ ጽዋ በጸጋ ለመቀበል ዝግጁ ነኝ ሲል የአንድነት ፓርቲ ም/ሊቀመንበር አንዱአለም አራጌ ለወያኔ ችሎት አስታወቀ

የአገሪቱን የፍትህ ሥርዓት ለስልጣን ዕድሜ ማራዘሚያ ጠባብ አላማው እየተገለገለ ያለው የዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ የሥልጣን ተቀናቃኞቹ አድርጎ በሚቆጥራቸው ተቃዋሚ ፓርቲ አባላትና ደጋፊዎች እንዲሁም ነጻ ጋዜጤኞች ላይ እንዲተላለፍ የፈለገው ይህ የጥፋተኝነት ብይን የተሰጠው በትናንትናው ዕለት በሽብርተኝነት ወንጀል ክስ በተከሰሱት በነ አንዱአለም አራጌ ላይ የከፍተኛ ፍርድ ቤት 3ኛ ወንጀል ችሎት የተባለው የካድሬ ዳኞች ባስተላለፉት ውሳኔ ነው።

የወያኔን ፍርድቤት ውሎ የተከታተለው የግንቦት 7 ዘጋቢ ከሥፍራው በላከው ዜና ይህ የጥፋተኝነት ብይን የተሰጠው ፤ የአረብ አብዮት ወያኔ ላይ በፈጠረው ጭንቀት ምክንያት ተመሳሳይ ህዝባዊ አመጽ ሊቀሰቅሱ ይችላሉ በሚል ስጋት ከየቤታቸው ታፍሰው ወያኔ እስር ቤት ከተወረወሩ ቦሃላ የሽብርተኝነት ክስ የተመሰረተባቸው ሁሉም ተከሳሾች ላይ ነው።

ይህንን ፖለቲካዊ ውሳኔ ለማስተላለፍ የሞራል ስብዕናና የሙያ ክብር እንደማያግዳቸው ታምኖባቸው በጥንቃቄ የተመደቡት ካድሬ ዳኞች የመሀል ዳኛው እንዳሻው አዳነ፣ ቀኝ ዳኛ ሙሉጌታ ኪዳኔ እና (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ግንቦት 7፣ የመለስ ዜናዊ የይስሙላ ፍርድ ቤት በትናንትናው እለት በአቶ አንዱዓለም አራጌ መዝገብ ያሳለፈውን ብይን አወገዘ

ግንቦት 7: የፍትህ፤ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ፣ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ የይስሙላ ፍርድ ቤት በትናንትናው እለት በ24 የፖለቲካ እስረኞች ላይ ያሳለፈው የጥፋተኝነት ብይን በተመለከተ መግለጫ አወጣ።

ግንቦት 7፣ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ባወጣው በዚሁ መግለጫው የመለስ ዜናዊ አሻንጉሊት የሆነው ፍርድ ቤት ሰጠሁ ያለውን ብይን "አሳፋሪ" ሲል ኮንኖታል። "የኢትዮጵያ ሕዝብ ከወያኔ ፍርድ ቤቶች ፍትህ ይገኛል ብሎ ተስፋ ስለማያደርግ የዛሬው ብይን የተጠበቀ ነበር" ያለው መግለጫ የፍትህ ሥርዓቱ መለስ ዜናዊ ተቀናቃኞቹ ያላቸውን ሁሉ ማጥቂያ መሣሪያ ማድረጉ ገልጿል።

የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ጋዜጠኞችን በማሰር ዓለምን እየመራ እንደሆነ የጋዘጠኞች መብት ተከራካሪ የሆነው ዓለም ዓቀፍ ድርጅት (ሲ.ፒ.ጄ) መግለጹ ያስታወሰው ይኸው መግለጫ የዛሬ ብይን ለነፃ ፕሬስና ጋዜጠኝነት ላይ እየተደረገ ያለው አፈና ተጨማሪ አመላካች ነው ብሏል።

እንደ አውሮፓዊያን አቆጣጠር በ2009 የወጣው "የፀረ-ሽብር ህግ" የሚባለው ህገወጥ ህግ ዓለም ዓቀፍ ተቀባይነት ያላቸውን ሰብዓዊ መብቶችን በሙሉ በመደፍጠጥ በሃሳብ የተለየን ዜጋ ማጥቂያ መሳሪያ መሆኑን የዓለም ማኅበረሰብ እንዲያውቀው መግለጫ አሳስቧል።

መግለጫው የኢትዮጵያ ሕዝብ ይህ በኢትዮጵያውያን ጫንቃ ላይ የተንሰራፋውን ግፈኛውን የመለስ አገዛዝ "በቃህ" እንዲለው ጥሪ አስተላልፏል። "መለስ ከሚገባው በላይ ፈንጭቶብናል፤ ኢትዮጵያዊያንም በመጠን በላይ ግፍ ተፈጽሞብናል" ያለው መግለጫው አሁን ሁላችንም መለስን "በቃህ" እንበለው ብሏል።

በመጨረሻም የኦባማ አስተዳደርና የበለጸጉ አገራት መሪዎች በኢትዮጵያ ላይ ግፍ እየተፈጸመ እያዩ እንዳላያዩ ማለፋቸውን እንዲተውና ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን እንዲቆሙ ጥሪ አድርጓል።

አሜሪካ የኢትዮጵያዊያንን ስቃይ ትመልከት፤ አምባገነንን መርዳቷ ታቁም ሲል መግለጫው አጠቃሏል።

## የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በረሃብተኞች ሥም ከምዕራባዊያን ለጋሾች በእርዳታ ያገኘውን ምግብ ከአገር ውጪ ለመሸጥ በዝግጅት ላይ መሆኑ ተዘገበ

በዘረኛውና አምባገነኑ መለስ ዜናዊ የሚመራው ህወሃት ከምዕራባዊያን የበጎ አድራጊ ድርጅቶችና መንግስታት በረሃብ ለተጎዳው ወገናችን የተላከውን የእርዳታ እሕል፤ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ድርጅት በተሰኘው ተቋም በኩል በአለም ዓቀፍ ገበያ አውጥቶ ለመሸጥ እንዳቀደ ሬውተር የተሰኘው የዜና ወኪል ዘገበ።

በቅርቡ ሃላፊነቴን ለሌላ ሰው አስረክባለሁ ያለቺው የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ድርጅት ዋና ስራ አስፈፃሚ ዶ/ር እሌኒ ገብረ መድሕን፤ በዚሁ ጉዳይ ዙሪያ ላነጋገራት ለሬውተር የዜና ወኪል እንደገለጸቺው ፤ በእርዳታ የተገኘውን እህል፤ በተለይም በቆሎና ስንዴ በድርጅቱ አማካኝነት ለሽያጭ በማቅረብ ከዚሁ በሚገኘው ገንዘብ የውሃ ጉድጓዶችን ለመቆፈሪያና፣ ለኤሌክትሪክ ሃይል ማስፋፊያ ለማዋል እንደታቀደ ተናግራለች። ሆኖም ዶ/ር እሌኒ ይህ እቅድ እንዴት እንደሚተገበር በዝርዝር ማስረዳት እልቻለቺም ሲል ሬውተርስ በዚሁ የዜና ዘገባው ጠቅሶአል።

ሂዮመን ራይትስ ወች የተሰኘው ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ተከራካሪ ድርጅት፤ ባሳለፍነው የፈረንጆቹ ዓመት ባወጣው መግለጫ እንደጠቀመው፣ 20 በመቶ የሚሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከውጭ አገር የሚመጣ እርዳታ ጠብቆ የሚኖር ሲሆን፣ ከ7 ሚሊዮን በላይ ህዝብ በመጠባበቂያ ምግብእርዳታ፣ ከ7-10 ሚሊዮን የሚሆነው ደግሞ በአስቸኳይ የምግብ እርዳታ ሕይወቱን እንደሚታደግ አስታውቆ ነበር።

በያዝነው ዓመትም 12 ሚልዩን የሚጠጋ ኢትዮጵያዊ ከወዲሁ አስቸኳይ የምግብ እርዳታ ካላገኘ በአገራችን አስከፊ እልቂት ሊከሰት እንደሚችል፣ ግብረ-ሰናይ ድርጅቶች ለዓለም ማሕበረሰብ ለማስገንዘብ እየጮሁ ባለበት ወቅት፣ ወያኔ፤ በጎ አድራጊዎች የሚመፀውቱትን የምግብ እርዳታ ሳይቀር ለውጭ ገበያ ለማቅረብ የያዘው ዕቅድ ብዙዎችን ያስገረመ ብቻ ሳይሆን ያስደነገጠ ሆኖ ተገኝቷል።

የቀድሞው የህወሃት የፋይናንስ ክፍል ሃላፊ አቶ ገ/መድህን አርአያን ጨምሮ ሌሎች ውስጥ አዋቂዎች ካሁን ቀደም እንዳጋለጡት፤ የሕወሃት ሹሞች ለስልጣን ከሙበቃታቸው በፊት ጀምሮ በረሃብ እየረገፈ ለነበረው (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

## የአዋሳው እሳት የወያኔ መጥፊያ ይሆናል!!!

ከአስር ዓመታት በፊት "ሲዳማ ክልል ሁና ትደራጅ" የሚል ጥያቄ በማቅረባቸው በአንድ ቀን ውስጥ ከ60 በላይ የሆኑ የአዋሳ ከተማ ነዋሪዎች በአጋዚ ጦር በግፍ ተጨፈጨፉ፤ በመቶዎች የሚቆጠሩ ለአካል ጉዳቶች ተዳረጉ፤ በርካቶች ታሰሩ። ከሰባት ዓመታት በፊት ደግሞ - በምርጫ 97 ማግሥት - "ድምፃችን ይከበር" በማለታቸው እስካሁን ቁጥራቸው በትክክል የማይታወቅ የአዋሳ ወጣቶች ተገደሉ፤ በርካታ ወጣቶችና አዛውንት ታሰሩ፣ ተደበደቡ፣ ተጋዙ።

ዛሬም አዋሳ በውጥረት ውስጥ ነች።

የመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ ሠራዊት እንደለመደው የአዋሳን እና የአካባቢው ነዋሪዎች ሊገድል፣ ሊያቆስል፣ ሊያስር ዘምቷል። ከአዋሳ ወጣ ብላ በምትገኘው አለታ ጭኮ የመለስ ዜናዊ ፓሊሶች ነዋሪዎችን ገድለዋል፤ በርካቶችን አቁስለዋል። ነዋሪዎችም በፓሊሶች ለደረሰባቸው ጥቃት በወሰዱት የመከላከል እርምጃ አንድ ፓሊስ ሕይወቱን አጥቷል። የሚሰማቸው ጀሮ አላገኙም እንጂ ሕዝብን ከሕዝብ በማጋጫት ሙያ የተካኑት የመለስ ካድሬዎች "አዋሳ ከተማ ወደ ፌደራል ትጠቃለል ያሉት ወላይታዎች ናቸው" እያሉ በማስወራት ላይ ናቸው።

መለስ ዜናዊ የፈጠረው ዘርን ብቻ መሠረት ያደረገው "ፌደራሊዝም" በማር የተለወሰ መርዝ መሆኑ ባለፉት ሃያ ዓመታት በተግባር ያየነው ጉዳይ ነው። የመለስ ዜናዊ የውሸት ፌደራሊዝም ከሁሉም የአገራችን ክፍሎች በባሰ የተሳለቀበት "የደቡብ ብሄር፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት" በሚባለው የአገራችን ክፍል ነው። አዋሳ ደግሞ የዚህ የአቅጣጫ ስያሜ የተሰጠው "መንግሥት" መቀመጫ ናት። አዋሳ እና እሷ የምትወክለው "የደቡብ ብሄር፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት" የመለስ ዜናዊ ፌደራሊዝም አስከፊ ገጽታ ማሳያዎች ናቸው። በመለስ ዜናዊ ፌደራሊዝም ምክንያት ውቧ አዋሳ የግጭቶች ማዕከል ሆናለች።

ይሁን እንጂ የአዋሳም ሆነ ሌሎች የክልሉ ነዋሪዎች የመለስ ዜናዊን ዘረኛ አደረጃጀት እና ዘረኛ አገዛዝ ተቀብለው አያውቁም። መምህር የኔሰው ገብሬ ኅዳር 4 ቀን 2004 ዓ.ም

*"በደል በዛ!!! ፍትህ በሌለበት አገር መኖር አልችም!!! በዚህ ሁኔታ መኖር ኑሮ አይባልም!!! ግፍና መከራ እያየሁ መኖር አልችልም!!!"*

ብሎ በራሱ ላይ ቤንዚን አርከፍክፎ የተሰዋባት ዋካ የምትገኘው በዚሁ ክልል በዳውሮ ዞን መሆኑ ማስታወሱ ብቻውን የክልሉ ሕዝብ ለመለስ ዜናዊ አገዛዝ ያለው የተቃዉሞ መጠን ገላጭ ነው። ከዚህም በተጨማሪ የአዋሳና የአርባ ምንጭ ተደጋጋሚ ሕዝባዊ አመፆች እና የቤንች ማጂ ዞን ነዋሪዎች የከርሰ ምድር ሃብታቸውን ለወያኔ ባለሃብቶች ላለመስጠት በማድረግ ላይ ያሉት ትንንቅ በአብነት ማንሳት ይቻላል። ደቡብ፣ በ1997 ምርጫ ወቅት የወያኔ ካድሬዎች እግራቸውን ማሳረፊያ ያጡበት ክልል እንደነበር ማስታወሱም ይጠቅማል።

በምርጫ 97 ወዲህ የመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ "በደቡብ" እግሩን ለመትከል በብርቱ ጥሯል፤ በተወሰነ መጠንም ፕረቱ ፍሬ አፍርቷል። ጥቅም እስካገኙ ድረስ ስለ ፍትህ፣ ነፃነት፣ እኩልነትና ዲሞክራሲ ደንታ የሌላቸው፤ የራሳቸውን የቤተሰብ አባላት ሳይቀር ለእርድ ለማቅረብ የማይሰቀጥጣቸው አድርባዮችን 'ከደቡብ" መመልመል ችሏል። እነዚህ ወራዳ የመለስ ምልምሎች ናቸው የአዋሳን እና የአካባቢውን ሕዝብ እርስ በርስ በማጣላት የሕዝቡን ፀረ-ወያኔ የትግል ትኩረት አቅጣጫ ለማስቀየር ተግተው ውሸቶችን እያሰራጩ ያሉት።

ይሁን እንጂ ከቀድሞው በባሰ ዛሬ ሲዳማው በወያኔ መሠሪ ተንኮል ተቀጥቷል። ወላይታውም የዚያኑ ያህል በወያኔ መሠሪ ተንኮል ተቀጥቷል። ሃድያው፣ ጉራጌው፣ ጋሞው፣ ከምባታው፣ ስልጢው፣ ሃመሩ፣ ሙርሲው .... "ደቡብ" በተባለ ቋት ውስጥ የገቡት የውዲቷና የዉቧ አገራች ልጆች በሙሉ በወያኔ ላይ ተንኮል ተቀጥተዋል። እናም የመለስ ዜናዊ ሎሌዎችሕዝብን ከሕዝብ ጋር ለማጣላት የሚደርጉት መሯሯጥ እነሱ የሚፈልጉትን ውጤት አያመጣም። ወያኔ በደቡብ የቆሰቆሰው እሳት መጥፊያው እንደሚሆን ምልክቶች እየታዩ ነው።

ግንቦት7፡ የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ፣ ወያኔ "የደቡብ ብሄር፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት" እያለ በሚጠራው የአገራችን ክልል ውስጥ የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን ሁሉ በትግራዩ ገገር ጉጅሌ መሠሪ ተንኮል ሳቢያ ዓይናቸውን ከዋነኛ ጠላታቸው ወያኔ ላይ እንዳይነቅሉ በጥብቅ ያሳስባል።

የኢትዮጵያዊያን ሁሉ የጋራ ጠላት የመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ ነው። ይህ ዘረኛ አገዛዝ ከተወገደ ችግሮቻችንን ሁሉ በምክክር መፍታት እንችላለን። ስለሆነም ዛሬ ትኩረታችን ሁሉ ወያኔ የጫነብንን ዘረኛ አገዛዝ አስወግደን ፍትህ፣ ነፃነትና ዲሞክራሲ የሰፈኑባት ኢትዮጵያን መፍጠር ነው።

መምህር የኔሰው ገብሬን ጨምሮ በርካታ የክልሉ ነዋሪዎች የተሰውት ስለኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት፤ ከዚያም አልፎ ስለ ሰው ልጅ ነፃነት መሆኑ ለአፍታም አንዘነጋም።

ወያኔ በአዋሳና አካባቢዋ ነዋሪዎች ላይ የቆሰቆሰው እሳት የራሱ የወያኔ መጥፊያው እንዲሆን ለማድረግ ተግተን እንድንሠራ ግንቦት 7 ጥሪ ያደርጋል።

በዚህ አጋጣሚም በእነዚህና መሰል ግጭቶች ሳቢያ ለሚጠፋው እያንዳንዱ የሰው ሕይወት በመለስ ዜናዊ የሚመራው የትግራይ ገዥ ጉጅሌ በኃላፊነት የሚጠየቅ መሆኑን ግንቦት 7 በጥብቅ ያስገነዝባል።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

---

## የዘረኛው መለስ ዜናዊ ፍርድ ቤት በነጻነት ታጋዮች ላይ የጥፋተኝነት ብይን አስተላለፈ። ከሳሾቹ እንድጠጣው የሚፈልጉትን የግፍ ጽዋ በጸጋ ለመቀበል ዝግጁ ነኝ ሲል ... (ከገፅ 1 የዞረ)

ግራ ዳኛ ሁሴን ይመር 3 ሰአት ከ40 ደቂቃ ላይ የተሰየሙ ሲሆን አቃቢ ህጎች ቴዎድሮስ ባህሩ፣ አንተነህ ጌታቸው፣ ዘረሰናይ ምስግናውና እና ብርሀኑ ወንድማገኝ እንዲሁም የተከላካይ ጠበቆች የሆኑት አቶ ተመስገን ደርበው፣ አቶ አበበ ጉታ እና የመንግስት ተቀጣሪ ጠበቃ አቶ ሳሙኤል አባተ ተገኝተዋል።

በዚህ የወያኔ የፈጠራ ክስ የአንድነት ፓርቲ ከፍተኛ የአመራር አባል የሆነው ወጣቱ ፖለቲከኛ አንዱአለም አራጌ እና አቶ ናትናኤል መኮንን፣ ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ እና የመኢዴፓ ፓርቲ አመራር የሆኑት አቶ ክንፈ ሚካኤል ደበበ በተከሰሱበት አንደኛ፣ ሁለተኛ እና አራተኛ ክሶች ጥፋተኛ ተብለዋል።

በክሱ ድራማ ላይ የወያኔ አቃቢ ህግ ሁሉም ተከሳሾች በጋራ ወንጀል በመንቀሳቀሳቸው እና ከፍተኛ የሀገር ጉዳት የሚያስከትል በመሆኑ እስከ እድሜ ልክ ጽኑ እስራት ከብዶ እንዲፈረድ የቅጣት ሀሳብ አቅርቧል።

ፍርድ ቤት ተብዬው የወያኔ ችሎት አቃቢ ህግ ያቀረበውን ክስ በሙሉ አጽድቆ የተቀበለ እና ተከሳሾችን ጥፋተኛ ብሎ የፈረደ ሲሆን በአንጻሩ ተከሳሾች አቃቢ ህግ ያቀረበባቸውን ክስ ማስተባበል ባለመቻላቸው ጥፋተኞች ናቸው ሲል ውሳኔ ሰጥቷል።

የአንዱአለም፣ ናትናኤል፣ እስክንድር እና አበበ ቀስቶ ጠበቃ አቶ ተመስገን ደርበው እና አቶ አበበ ጉታ ደንበኞቹ ራሳቸው የቅጣት ውሳኔ እንዲሰጡ መጠየቃቸውን ተከትሎ ፣ ፍርድ ቤቱ የአንዱአለምን ንግግር ለመስማት ተገዷል። አንዱአለም " እኔ ምንም የፍርድ ቅጣት ሀሳብ የለኝም፣ ለልጆቼና ለኢትዮጵያውያን ሁሉ ዴሞክራሲና ነፃነት እንደሚገባን በማመን አቅሜ በፈቀደው መጠን ታግያለሁ:: ይኼን በማድረጌ በማንም ላይ በክፋት አልተነሳሁም፤ ይኼን በማድረጌ ህግ ጥሼ አላውቅም፤ ይኼን በማድረጌ በደሃዋ ሃገሬ ጥቅም ላይ አልተነሳሁም፤ ይሄን በማድረጌ ፈጣሪዬን፣ የኢትዮጵያን ህዝብም ሆነ ህሊናዬን የሚያሳዝን አንዳች ነገር ፈፅሜያለሁ ብዬ አላምንም:: ፍፁም ሰላም ይሰማኛል:: እኔን እዚህ ያቆመኝ የነፃነት ናፍቆት ነው:: በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶችም ፍትህን ለምኜ ስነፈግ ይኼ የመጀርያዬ አይደለም:: ከሳሾቹ እንድጠጣው የሚፈልጉትን የግፍ ፅዋ በፀጋ ከመጠጣት ውጪ ባልፈፀምኩት ወንጀል ማቅለያ የመጠየቅን አማራጭ ህሊናዬ ስላልተወልኝ አዝናለሁ" በማለት በጊዚያዊ ጥቅም ተደልለውና የሞራል ዝቅጠት ውስጥ ሆነው የተከበረውን የዳኝነት ተግባር በማራከስ ሥራ ላይ ለተሰማሩት ዳኞችና አቃቤ ህግ ተብዬዎች ከሂሊና ውስጥ የማይጠፋ ንግግር አሰምቶአል::

ካድሬ ዳኞቹ በመቀጠል የየራሳቸውን ሃሳብ ለመስጠት በዝግጅት ላይ የነበሩትን ጋዜጠኛ እስክንድ ነጋን፣ ናትናኤል መኮንንና ክንፈሚካኤል በረደድን ንግግር እንደጀመሩ አስቆሟቸዋል። ጋዜጠኛ እስክንድር "እባካችሁ ዳኞች የሚጠብቀን ፍርድ እስከ ሞት የሚያስቀጣ በመሆኑ አቃቢ ህግን በግልጽ ችሎት አነጋገራችሁ እኛን እድሉን አትንፈጉን፣ 2 ደቂቃ ብቻ ልናገር፣ የፍትህ ሚዛኑን ጠብቁ፣" በማለት ቢናገርም ለሂሊናቸው ሳይሆን ለሆዳቸው ከፍተኛ ክብር የሚሰጡ ዳኞች በፖሊስ እንዳይናገር አስቁመውታል።

ከዚህ ቦሃላ የመጨረሻውን የፍርድ ውሳኔ ለመስጠት ለሀምሌ 6 ቀን 2004 ዓም ተለዋጭ ቀጠሮ ተሰጥቶ ችሎቱ ተበትኖአል።
በችሎቱ ላይ በርካታ የአገር ውስጥና የውጭ ጋዜጠኞች፣ የአሜሪካን አምባሳደር ጨምሮ የበርካታ አገራት ዲጵሎማቶች እና የእስረኞች ቤተሰቦች ተገኝተዋል።

ተከሳሾችን ሁሌም እንደሚደረገው በጓሮ በር በኩል ወጥተው በጓሮ በር በኩል ተመልሰዋል።

ሂውማን ራይትስ ወች የጸረ ሽብር ህጉ ሀሳብን በነጻነት የመግለጥን መብት ለመደፍጠጥ ጥቅም ላይ እየዋለ ነው በሚል ርእስ ባወጣው መግለጫ፣ የፍርድ ሂደቱን እና ውሳኔውን ክፉኛ ተችቶአል። ለጋሽ አገራት ውሳኔውን እንዲያወግዙና የፍትህ ስርአቱ እንዲሻሻል ጫና እንዲያደርጉ ጠይቋል።

የሂውማን ራይትስ የአፍሪካ ም/ል ዳይሬክተር የሆኑት ሊስሌ ሊፍኮው የኢትዮጵያው አገዛዝ መጠነኛ የሚባሉ ትችቶችን እንኳን ለመታገስ አቅም እያጠረው እንደመጣ ተናግረዋል።

---

# እናንተ “እኔ ገለልተኛ” ነኝ የምትሉ ሆይ ስሙ !!!

ሁለት ጎረቤቶች ባንዳች ምክንያት ባይግባቡና በመሃከላቸው ጥል ቢኖር ያንን ለመሸመገል ገለልተኛ ሁኖ ነገሮችን ለማየት መሞከር የአስተዋይ ሰው ጠባይ ነው። አንዱ ህግ የማይገዛው ጉልበተኛ ግን ደካማውን ሲረግጥ እና ሲያንገላታ እያዩ “እኔ ገለልተኛ ነኝ “ማለት ግን የጨዋ ሰው ልማድ ሁኖ አይቆጠርም። እንዲያውም የራስ ወዳዶች እና የሰው ልጆች ስቃይ ግድ የማይላቸው ግለሰቦች መገለጫ እንጂ።

አሁን የኤልዛቤልንና የናቡቴን ታሪክ ልናስታውስ ወደናል።

በእስራኤል ምድር ብዙ በደል የፈጸመች ኤላዛቤል የምትባል ንግስት ነበረች። ከፈጸመቻቸው በደሎች መካከል የከፋው ናቡቴ የተባለውን ድሃ ገበሬ ማስገደሏ ነበር። ናቡቴ ወይን የሚያመርትባት ጥሩ ለም መሬት ነበረችው።የኤልዛቤል ባል የነበረው ንጉስ አክአብም የናቡቴን ለም መሬት አይቶ ወደዳት ይወስዳትም ዘንድ ተመኝቶ እንዲሰጠው ናቡቴን ጠየቀው። ሊነጥቀው ሙሉ መብት እያለው ስጠኝ ብሎ መለመኑ የየዋህ አምባገነን መገለጫ ነው። ናቡቴ ግን የአባቶቼን መሬት እስጥ ዘንድ አይሆንም አለ። አክአብም እጅግ አዝኖ ምግብም አልበላም መጠጥም በአፌ አይዞርም አለ።ሃዘኑን ያየች ኤልዛቤልም የናቡቴን መሬት ወስዳ ለባሏ ልትሰጥ ቆርጣ ተነሳች። ናቡቴንም በሃሰት አስከስሳ ምናምንቴ ሰዎችን ምስክር አቁማ በሞት እንዲቀጣ አስደረገችው። ድሃው ናቡቴ የአባቶቼን መሬት እባካችሁ ተውልኝ ልጆቼንም ላሳድግበት ቢል ሰሚ አጥቶ ተወግሮ ተገደለ።መሬቱንም አልዛቤል ወሰደችበት።

በዚያ ዘመን አንድ በእውነት እግዚአብሄርንም የሚፈራ ጨዋ ነብይ ነበር። ይህ ነብይ እንዲህ ኢፍትሃዊ ድርጊት በኤልዛቤል ሲፈጽም አይቶ ዝም አላለም። ንጉሱንም የንጹህ ሰው ደም አፍሰሃል ብሎ በብርቱ ገሰጸው። ኤልዛቤልንም ውሾች ደምሽን ይሉሳታል ሲል ተነበየባት። ነብዩ እንዳለውም ኤልዛቤል የድሃውን ደም አፍስሳ ስታበቃ ሞተች እና ውሾችም ደሟን ላሱት። የሚቀበርም ስጋ አላተረፉም።

ዛሬ በአገራችን ኤልዛቤልን የመሰሉ የድሃ ንብረት የሚዘረፉ እና የንጹሃንን ደም እንዲሁ በከንቱ የሚያፈሱ ነግሰዋል። የሃይማኖት አባቶች/መሪዎች ነን የሚሉም ከመቸውም ግዜ በላይ በኢትዮጵያ በዝተው እየታዩ ነው።ብዙ እግዚአብሄርን እንፈራለን የሚሉ ምእምናንም አሉ። የሃይማኖት አስተማሪዎች/መሪዎች ነን የሚሉ እንደ አሸን በፈሉበት አገር ውስጥ የኤልዛቤል መንፍስ ነግሶ ናቡቴን የመሰሉ የብዙ ንጹሃን ዜጎች ደም እንዲሁ በከንቱ እየፈሰሰ ነው።

ብዙ ኢትዮጵያዊያን ገበሬዎች የአባቶቻችንን መሬት አንሰጥም በማለታቸው ተገድለው ተቀብረዋል።ከሞት የተረፉትም ሜዳ ላይ ተጥለው ለልመና ተዳርገው በአይናችን አይተናል በጆሮአችንም ሰምተናል። ብዙ ዜጎችም በሃሰት ተመስክሮባቸው በሞት እንዲቀጡ መደረጉንም እናውቃለን።በኢትዮጵያ ምድር የብሮችን መልክ ለይቶ የማያውቅ ህጻን ባንክ ሊዘርፍ ነበር ተብሎ በጥይት ተደብድቦ በአዲስ አበባ ምድር መገደሉን አይተናል።በኢትዮጵያ ምድር ዜጎች ዘራቸው እየተቆጠረ ተገድለው ጉድጓድ ውስጥ መጨመራቸውን ያልሰማ የለም። መለስ ዜናዊ “አማራ የትግራይ ህዝብ ቀንደኛ ጠላት ነው “ብሎ የጻፈውን ኢትዮጵያዊያን በያሉበት አይተዋል። ከኢትዮጵያ ምድርም ብዙ ወንዶችና ሴቶች ልጆች ተሰደው የበርሃ እና የአዞ ሲሳይ መሆናቸውንም ያልሰማ የለም።

በገዛ አገራቸው የሚፈጸምባቸውን በደል ሸሽተው በሚሰደዱ ወገኖቻችን ላይ እየደረሰ ያለው በደልና ውረደት በታየና በተሰማ ግዜ ኢትዮጵያዊያን በሃፍረተ ተሸማቀናል። እንደ ቀድሞ አባቶቻችንም አንገታችንን ቀና አድርገን ሰው መሃል ለመቆም በማንችልበት ደረጃ ላይ ደርሰናል። እንዲህ ዓይነቱን ውረደት ከማይ ብለው ራሳቸው ላይ ጋዝ አርከፍክፈው ተቃጥለው የሞቱ ኢትዮጵያንም የሚረሱ አይደሉም። በአጠቃላይ አነጋገር በመለስ ዜናዊ እጅ ያለችው አገራችን በጽኑ ደዌ ተይዛለች።

እንግዲህ ኢትዮጵያዊያን መከራቸው በዝቶ፤በገዛ አገራቸው የመኖር መብት ተነፍገው ሳይወዱ በግድ ከቀያቸው ተነቅለው ሲሰደዱ፤አገርም ባዶዋን ስትቀር እያዩ “እኔ አያገባኝም፤እኔ ገለልተኛ ነኝ” ማለት የጨዋ ሰው ተግባር አለመሆኑን አጥብቀን እንነግራችኋለን። ጨዋ ሰው ድሃ ሲበደል ፤ህግ ቂም መወጣጫ ሲሆን፤ ፍትህ ሲጓደል እያየ “እኔ ገለልተኛ ነኝ፤ እኔ አያገባኝም “ አይልም።ጨዋ ሰው እንዲህ ዓይነት በደል በወገን ላይ ሲፈጸም ሲያይና ሲሰማ በሙሉ እስትንፋሱ ይቃወማል እንጂ እኔ አልነካካም አይልም። ጨዋ ሰው አቅም አልባ ዜጎች በአጉራ ዘለሎች የማይበደልበት ሥርዓት እንዲሰራ በርትቶ ይታገላል እንጂ አይቶ እንዳላየ፤ ሰምቶ እንዳልሰማ አይሆንም።

ዛሬ ኢትዮጵያችን ከመቸውም ግዜ በበለጠ ሁኔታ የወገኖቻቸው ስቃይ የሚያሰቃያቸውን ቅን ልጆቿን ትጣራለች።የድሃ በደል የሚቆጫቸውን ልጆቿን ከመቸውም ግዜ በላይ አሁን ትፈልጋለች። ሂሊና የሌለው ግመል እርግቦችን ረግጦ እያንጫጫ እና “ግመሉም ይሄዳል ውሾችም ይጮሃሉ” እያለ ሲፎክር እያያችሁ “እኔ ገለልተኛ ነኝ” የምትሉ ሆይ ስሙ በምንም ሁኔታ እርግቦቹ ይቅር አይሏችሁም። ዛሬ ብዙ ኢትዮጵያዊያን እንደ እርግቦቹ ተረግጠው እየተሰቃዩ ነው። ይሄን እያያችሁ እኔ አያገባኝም እኔ ገለልተኛ ነኝ የምትሉ የቆማችሁትን ምድር ታስተውሉ ዘንድ እንመክራችኋለን።

አገሪቷ እንዲህ በጽኑ ደዌ ተይዛ ባለችበት በዚህ ዘመን “እኔ አልነካካም !!! እኔ ገለልተኛ ነኝ !!! የምትሉ ኢትዮጵያዊያን ከትግራዩ ገዥ ጉጅሌ በምን እንደምትለዩ ራሳችሁን ትመረምሩ ዘንድ ደግመን እናሳስባችኋለን። የአገሪቷ ዜጎች እንባ እንደ ራሄል እንባ ጠርዙን ሞልቶ እየፈሰሰ ባለበት በዚህ ዘመን፤ ኢትዮጵያችን የሰው ያለህ ብላ በምትጮኽበት በዚህ ዘመን “እኔ ገለልተኛ ነኝ” የምትሉ ነገ የታሪክ ተወቃሾች ናቸው። ታሪክ የሚያስታውሳችሁ በአገሪቷ የመከራ ወቅት ከጠላት ጎን መቆማችሁን እንጂ ጠላትን ተው ለማለት መነሳታችሁን አይደለም። እኛም ከትግራዩ ገዥ ጉጅሌ ለይተን አናያችሁም። አገር ስትፈርስ እያያችሁ እኔ አያገባኝም የምትሉ ከአፍራሾቹ በምን እንደምትለዩ እኛ አናውቅም።

በመጨረሻም “እኔ ገለልተኛ ነኝ”ን ልማድ ያደረጋችሁ፤ በተለይ የሃይማኖት መሪዎች ሆይ የታላቁን ሰው አልበርት አንስታይንን ምክር ስሙ።እንዲህም ይላችኋል”*ዓለማችን የምትጠፋው ክፉ በሚያደርጉ ሰዎች ሳይሆን፤ ክፉ ሲያደርጉ እያዩ ዝም በሚሉ ሰዎች ነው”*።እናንተ “ገለልተኛ ነኝ፤ እኔ አልነካካም” የምትሉ መንታ መንገድ ላይ የቆማችሁ ሆይ ልብ ብላችሁ የአልበርትን አባባል አሰላስሉ።ማህተመ ጋንዲም እንዲህ ይላችኋል *“አንድን ክፉ ሥርዓት ደህና አድርገህ የምታጠናክረው ትእዛዙን እና የሚያወጣውንም ህግ እሺ ብለህ ስትቀበል ነው።ክፍ ሥርዓት እንዲህ ዓይነት ታዛዥነት አይገባውም።ለዚህ ዓይነቱ ሥርዓት መታዘዝ ማለት የክፋቱ ተባባሪ መሆን ማለት ነው።ማንኛውም መልካም ሰው ክፉውን ሥርዓት በሙሉ ልቡ ይቃወማል።” ብለዋል ማህተመ ጋንዲ* ።እንግዲህ ከዚህ በኋላ የምንጨምረው እነ መለስ ዜናዊ በአገራችን ላይ የሚፈጽሙትን ክፋት የምትቃወሙ ሁኑ እንጂ እያያችሁና እየሰማችሁ ዝም የምትሉ አትሁኑ።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ !!!**

**እግዚአብሄር ኢትዮጵያን ይባርክ !!!**

## የደቡብ ሱዳን መንግስት 14 የአኙዋክ ብሄረሰብ ተወላጆችን ለወያኔ መንግስት አሳልፎ ሰጠ

የዘረኛው ወያኔ አገዛዝ ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት ሚኒስትር ደኤታ ሽመልስ ከማል እንደገለጸው ሰዎቹ ተላልፈው የተሰጡት ሁለቱ መንግስታት ባላቸው የጠረጠሩትንና የፈለጉትን ሰው አሳልፎ የመስጠት ስምምነት ነው።

እናም እነኚሁ የአኙዋክ ስደተኞች በወያኔ መንግስት ወታደሮች እንደተገደሉ ለሚጠረጠረውየ 19 ንጹሀን ዜጎች ፍጅትና በሳውዲ ስታር ኩባንያ ላይ ለተሰነዘረው ጥቃት ተጠያቂ እንደሚሆኑ ሆድ አደሩ ሽመልስ ከማል ገልጿል። ሽመልስ እንዳለው ወደ ደቡብ ሱዳን ሊሰደዱ የነበሩት እነዚህ የአኙዋክ ተወላጆች ከወያኔ ወታደሮች የድንበር ማዘዣ ጣቢያ አምልጠው ደቡብ ሱዳን ገብተው ነበር ይሁንና የተወሰኑት በደቡብ ሱዳን ወታደሮች ሲገደሉ 14ቱ ተይዘው ተመልሰዋል።

ለወያኔ ወንጀል መሸፋፈኛነት የተዘጋጁት እነዚህ ምስኪን የአኙዋክ ተወላጆች በአሁኑ ወቅት ምርመራ እየተካሄደባቸው እንደሆነና በቅርቡም ለፍርድ እንደሚቀርቡ ሽመልስ አክሎ ተናግሯል። በዚህ ጉዳይ ላይ ዘጋቢያችን ያነጋገራቸው አንድ የክልሉ ተወላጅ ስለ ሁኔታው በሰጡት አስተያየት የወያኔ መንግስት በቅርቡ በጋምቤላ የሚካሄደውን የሰብዓዊ መብት ጥሰትና የመሬት መቀራመት በመቃወም በክልሉ የሚካሄዱ ተቃውሞዎችን ለማፈንና ለማስፈራራት በርካታ የግፍ ርምጃዎችን እየወሰደ ይገኛል።

ይህም ንጹሀንን የማፈን ሴራ የዚሁ የግፍ ርምጃ አንድ አካል ሲሆን ባለፈው የደረሰውን የ19 ሰዎች ግድያና በክልሉ መሬት ዘረፋ ላይ በተሰማራው የሳውዲ ስታር ኩባንያ ላይ የደረሰውን ጥቃት ተበቅያለሁ ለማለትና ከእንግዲህም ምንም ዓይነት ተቃውሞ ብታሳዩ በዝርያችሁ ላይ ተመሳሳይ የበቀል ርምጃ እወስዳለሁ ለማለት ነው ብለዋል።

## የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በረሃብተኞች ሥም ከምዕራባዊያን ለጋሾች በእርዳታ ያገኘውን . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

የትግራይ ሕዝብ ከበጎ አድራጊ ድርጅቶች የተመፀወተውን የምግብ እርዳታ፣ በድብቅ ዞር አድርገው በመቸብቸብ ይጠቀሙ እንደነበር አጋልጠዋል። አሁንም በዚሁ መልኩ ለችግረኛ ወገናችን የመጣውን እርዳታ በይፋ ለመሸጥ ማቀዳቸውን ተከትሎ፤ ለጋሽ ድርጅቶችና መንግስታት ያደርጉ የነበረውን የምግብ እርዳታ ሊቀንሱ አንዳንዶቹም ጨርሶ ሊተውት ይችላሉ የሚለውን ስጋት ብዙዎች ይጋሩታል።

በቀድሞው የወያኔ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር አዲሱ ለገሰ የቦርድ ሊቀመንበርነት የሚተዳደረው የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ድርጅት፣ ቤተመንግስቱ ድረስ የሚዘረጋ ረጅም እጅ ያለው በሙስና የተጨማለቀ ተቋም እንደሆነ በተደጋጋሚ ይነገርለታል።

((ወደ ገጽ 4 ዞሯል))

## በኢትዮጵያ ውስጥ ዛሬም ለውጥ መምራት የሚችል አመራር እንደሌለ የወያኔው ተላላኪ ጁነዲን ሳዶ ገለጸ

የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስትር ተብዬው ጁነዲን ግኡዙ እየተባለ ለሚጠራው ፓርላማ ፈራ ተባ እያለ ባቀረበው ሪፖርት አስፈጻሚው አካል ለውጥ ለመምራት ቢንቀሳቀስም ገና ቁርጠኝነትና ብቃት ይጎድለዋል ሲል ገልጿል። በዚህ እርስ በእርሱ በሚጋጭ ሪፖርት አንዴ ለመምራት ተንቀሳቅሷል፤ሌላ ጊዜ መምራት አልቻለም በማለት ሲገለጽ የቆየው ሚኒስትሩ አመራሩ የተገልጋዩን እርካታና ቅሬታ ከግምት ያላስገባ አገልግሎት እየሰጠ መሆኑን በመግለጽ ከእውነታው ጋር መፋጠጥ ግድ ሆኖበታል። በማከልም የኪራይ ሰብሳቢነት ምንጮች የሚባሉ ዘርፎችንም ጠቋቁሟል።እነርሱም ከመሬት አስተዳደር ፣ ከገቢ ሰብሳቢ፣ ከበጀትና ከንግድ ዘርፎች ጋር የተያያዙ ናቸው።

ሪፖርቱን አስመልክቶ የግንቦት 7 ዘጋቢ ያነጋገራቸው አቶ ሰይፉ የተባሉ የአዲስ አበባ ነዋሪ ሲገልጹ ጁነዲን ለውጥ መምራት የሚችል አመራር የለም ሲል በሌላ አነጋገር አገሪቱን መምራት የሚችል አመራር የለም ማለቱ ነው። ይህ ደግሞ ከወሬ በዘለለ በተግባር የሚታይ ለውጥ አለመኖሩን የሚያመላክት ነው። የዚህ ምክንያቱ ደግሞ በለውጥ ስም የወያኔ ደጋፊ ያልሆኑ ባለሙያዎችን ከስራ በማባረር አስፈጻሚ መስሪያ ቤቶችን በአቅመ ቢስ ታማኞች የመሙላት ውጤት ነው ብለዋል።

ሌላው አስተያየት ሰጪ በበኩላቸው ከአቅም ሌላ የቁርጠኝነት ችግርም አለ ነው የሚለው ይህም የወያኔ ካድሬዎች ተራ ሆድ አደር መሆናቸውን ከማሳየቱም ሌላ ምቾታቸው ከተጓደለ በማንኛውም ሰዓት እንደሚከዱት ማረጋገጫ ነው።በመሆኑም ሪፖርቱ በዘመነ ወያኔ አገሪቱን ከማትወጣው የችግር አዙሪት ውስጥ እየገባች እንደሆነ የሚያሳይ ነው ሲሉ አብራርተዋል።

የወያኔው ቁንጮ መለስ ዜናዊ ካድሬዎቻችን የወያኔን ዓላማ እስካስፈጸሙ ድረስ እውቀት ባይኖራቸውም አመራር ቦታ ላይ እናስቀምጣቸዋለን ማለቱ ይታወሳል።

## የአፋር አርብቶ አደር ህዝብ በሶማሊያ ክልልዊ መንግስት በሚሰነዘርበት ጥቃት፣ በወያኔ አገዛዝ የመሬት መቀራመት ፖሊሲና በአካባቢ ተፈጥሮ ሃብት መመናመን ከተለያየ አቅጣጫ ተቀስፎ በመያዙ ህልውናው አደጋ ላይ መውደቁን የአፋር ፎረም ሰሞኑን ባወጣው መግለጫ አስታወቀ

ድርጅቱ በዚሁ መግለጫው በአሁኑ ወቅት የአፋር ህዝብ ደህንነት በከፍተኛ አደጋ ውስጥ በመሆኑ ትግሉ የህልውና ሆኗል ብሏል።

መግለጫው በማከልም በተለይም በጸሎት ላይ ያሉ የ 70 ዓመት አዛውንትና ሁለት ታዳጊዎችን በመግደል የተጀመረው የሰሞኑ ጥቃት የሰለጠኑና በደንብ የታጠቁ የሶማሌ ክልል ሚሊሺያዎች በሚሰነዝሩት ጥቃት ተባብሶ ቀጥሏል።በዚህ ጥቃት በርካታ ንጹሀን ሲቪሎች ሲገደሉ ሌሎች በቁጥር የበዙ ለአካል ጉዳት ተዳርገዋል። ይህም ሆኖ ጥቃቱ የሚፈጸመው በወያኔ ፌደራል መንግስት ወታደሮች ፊት መሆኑና ወታደሮቹም የአፋርን ህዝብ ከጥቃቱ ለመከላከል የሚያደርጉት አንዳችም እንቅስቃሴ አለመኖሩ ይልቁንም ህዝቡ ራሱን እንኳን እንዳይከላከል እንቅፋት መሆናቸው ድርጊቱን አስገራሚ አድርጎታል ሲል አብራርቷል።

ቀደም ሲል በባለሙያዎች ሲነገር የቆየው የአፋርና ኢሳ ህዝቦች ግጭት ምክንያት የግጦሽ መሬት እጥረት ነው የሚለው አስተሳሰብ ዛሬ ተቀይሯል፤ግልጽ የሆነ ፖለቲኮ-ኤኮኖሚ ባህሪ ከክልል ጥያቄ ጋር ተቀናጅቶ ሌላ ገጽታ ሰጥቶታል - እንደ መግለጫው።

መግለጫው እንደሚለው በሶማሌ ክልላዊ መንግስት የሚደረገው ይህ የመስፋፋት ወረራ የታወቁ ፖለቲካዊና ኤኮኖሚያዊ ግቦች ያሉት ፤ይኸውም ከአፋር ክልልና ከኦሮሚያ ክልል መሬት በወረራ በመያዝ አዲስ የሸንሌ ክልላዊ መንግስት መመስረትን ፖለቲካዊ ግቡ ያደረገና ህገ ወጥ ቁሳቁሶችን ከጅቡቲ ወደ መሃል ሀገር በማስገባት ኤኮኖሚያዊ ጥቅም ማግኘትን ያካተተ ነው።

ይሄ ሁሉ ታዲያ የወያኔ አግዛዝ በሁለቱ ጎረቤታም ህዝቦች መካከል የሚነሱ ግጭቶችን በማስፋትና በማቀጣጠል የሚያባብሰው ነው የሚለው መግለጫው ምክንያቱ ደግሞ የህዝቡን ስሜት በሁለቱ የዳር ሀገር ህዝቦች ግጭት በመሳብ በመሀል ሀገር ሰላም ማግኘት ላይ ያነጣጠረ ነው ብሏል።

በመጨረሻም የአፋር ፎረም ሁለቱ ጎረቤታም ህዝቦች በሰላም የሚኖሩበት ሁኔታ እንዲፈጠር የሚደግፍ መሆኑን በመግለጽ የሸንሌ ዞን የአፋርን መሬት ይገባኛል ጥያቄ እንዲያቆም፣ የጅቡቲ መንግስት የሚያደርገውን ወታደራዊና የፋይናንስ ድጋፍ እንዲያቋርጥ፣ የወያኔ አገዛዝና የአፋር ክላላዊ መንግስት በአፋርና ኢሳ ህዝቦች መሬት መካከል ግልጽ የድንበር ማካለል ስራ እንዲሰሩ፣አለም አቀፉ ማህበረሰብም ደም መፋሰሱ እንዲቆምና ግጭቱ እንዳይባባስ ለማድረግ የሚያስችል ትርጉም ያለው መፍትሄ እንዲገኝ በሚችለው ሁሉ እንዲያግዝ ጥሪ አስተላልፏል።

## በደሴ ከተማ የሚኖሩ ሙስሊሞች ሰኔ 12 ቀን 2004 ዓ.ም ያዘጋጁት የህብረትና የበጎ አድራጎት ፕሮግራም እንዲሳካ ድንኳን በትውስት በመስጠት ያልተቆጠበ ድጋፍ ላደረጉት የአካባቢው ቤተክርስቲያን አባት ምስጋና አቀረቡ። በሌላ በኩል ይህ ፕሮግራም እንዲደናቀፍ ያልተሳካ ሙከራ ያደረጉት የአካባቢው ባለስልጣናት ድርጊት እንዳሳዘናቸው ገለጹ

አወሊያ ኦንላይን እንደገለጸው በዚህ በፍጹም ስኬት በተከናወነው ፕሮግራም ላይ አዘጋጁ ባደረጉት ንግግር ቤተክርስቲያን ፕሮግራማችን በስኬት እንዲጠናቀቅ ላደረገችው የበኩሏ ድጋፍ ያለኝን አድናቆትና አክብሮት ልገልጽ እወዳለሁ ብለዋል።

እንዲህ ዓይነቱ የሙስሊሞችና የክርስቲያኖች መደጋገፍ በኢትዮጵያ የተለመደ ተግባር ነው።እናም ይህ የሁለቱ ሃይማኖቶች የመደጋገፍ ባህል በዚህ ህብረትና መደጋገፍ ወሳኝ በሆነበት ወቅት ለሁላችንም ህብረት ለምንሻ ኢትዮጵያዊያን ጠንካራ መልዕክት የሚያስተላልፍ ነው።

በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች የበጎ አድራጎትና የህብረት ፕሮግራሞችን እንዲሁም ሀገሪቱን ከአህባሽ ችግር እንዲጠብቃት የጸሎት ስርዓቶችን በተከታታይ እያካሄዱ ይገኛሉ።ምክንያቱ ደግሞ እነሱ እንደሚሉት ይሄ አህባሽ የሚባለው ሊባኖሳዊ መሰረት ያለው አይዲዎሎጂ ለሀገሪቱ መረጋጋት ፈተና የሆነና በሙስሊሙ ህብረትና ተቋም ላይ የተሰነዘረ ጥቃት ነው።

የወያኔ አገዛዝ ፣ምንም እንኳን ቢክድም ይህንን የአህባሽ አይዲዎሎጂ በግምባር ቀደምትነት የሚቃወሙትን ወገኖች በተለያየ ስም በመወንጀል ከመስጊድ አካባቢ እንዲርቁና ሃይማኖታዊ ተግባራቸውን እንዳያከናውኑ በተደጋጋሚ እየጠየቀ ይገኛል።

በሌላ በኩል የአካባቢው የወያኔ ሹመኞች ለዝግጅቱ እንጀራ ለማቅረብ የተዋዋሉትን ወገኖች ውሉን እዲያፈርሱ በማስገደድ ፕሮግራሙ እንዳይሳካ ለማድረግ ያደረጉት ጣልቃ ገብነት እንዳሳዘናቸው የገለጹት አዘጋጆቹ በሹመኞቹ ድርጊት የተቆጡ በጎ ፈቃደኞች ከራሳቸው እንጀራ በማቅረብ የማደናቀፍ ሙከራውን መና አስቀርተውታል።

በተጨማሪም ከ 60 ሺህ በላይ የተቆራረጠ ዳቦም የነበረ በመሆኑ ፕሮግራሙ እጅግ ስኬታማ ነበር ብለዋል።

የሙስሊሙ ማህበረሰብ የወያኔ አገዛዝና የህገወጡ እስልምና ምክር ቤት አባላት ፍላጎት የሆነውን የአዲሱ እስልምና ምክር ቤት አባላት ምርጫ በቀበሌ መከናወን እደሚቃወምና ምርጫው ያለ መንግስት ጣልቃገብነት በመንፈሳዊ ስነ ስርዓት በመስጊዳች ውስጥ እንዲካሄድ እንደሚፈልግ ፣እንዲሁም የወያኔ አገዛዝ ባለስልጣናትና አፍቃሪ ወያኔ ሚዲያዎች የሙስሊሙን የመብት ጥያቄ በማዛባትና መሰረተ ቢስ ፍርሃት በመፍጠር በጎውን የኢትዮጵያዊያን ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች ግንኙነት ለማደፍረስ የሚያደርጉትን ሙከራ ማውገዙም መዘገቡ ይታወሳል።

## የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በረሃብተኞች ሥም ከምዕራባዊያን ለጋሾች በእርዳታ ያገኘውን . . . (ከገፅ 3 የዞረ)

ከወራት በፊት የዓለም ባንክ ለኢትዮጵያ ሊሰጠው አቅዶት ከነበረው 5 ሚልዮን የሚጠጋ ገንዘብ ውስጥ፤ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ 4 ሚሊዮን 8 መቶ ሺህ የአሜሪካን ዶላሩን የድርጅቱን አቅም ለመገንባት በሚል ሰበብ ዶ/ር እሌኒ ገብረመድህን ለሚትመራው ተቋም እንዲሰጥ ጠይቆ ነበር። ሆኖም ዶ/ር እሌኒ "ሚልንየም አይቲ" ከተሰኘው የስሪላንካ ድርጅት ጋር በመመሳጠር አሸንፌአለሁ ሲትል ያቀረበቺውን የጨረታ ኮንትራት፤ የሃሰት ድራማ መሆኑን የአለም ባንክ አስቀድሞ ስለደረሰበት፣ እርዳታውን ሙሉ ለሙሉ መሰረዙን በወቅቱ መዘገባችን ይታወሳል።

በያዝነው የፈረንጆቹ አመት መጀመሪያ ላይም "የአገራችን ቡና ላኪዎች ወደ ውጭ አገር የምንልከው ቡና አጥተናል፤ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ በኩል ግብይት የተፈጸመበት ቡናም ከመሃል አገር ወደ ኬንያ፣ ሱዳን፣ እንዲሁም ኤርትራ በሕገወጥ መንገድ እየተጫነ ነው።" በማለት አቤቱታቸውን አሰምተው ነበር። በዚህ ድርጅት በኩል ለውጪ ገቢያ ሊቀርብ የተዘጋጀ ከአስር ሺህ ቶን በላይ የተጣራ ቡናም በድንገት ከመጋዘን ጠፋ መባሉን ተከትሎ መለስ ዜናዊ "የአሁኑን እንተወው ከኣሁን በኋላ ግን በእንደዚህ ኣይነት ተግባር ላይ የሚሳተፍ እጁ ይቆረጣል" በማለት ጥፋተኞቹ እንዳይጠየቁ ጉዳዩን አለባብሶ ማለፉ በሰፊው መዘገቡ ይታወሳል።

### የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።

<u>መካከኛ ሞገድ</u>:- በ 358 MB, በ 837 kHz
<u>አጭር ሞገድ</u>:- በ 31 MB በ 9700 KHz
**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**
**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

<u>ማሳሰቢያ</u>:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org